# ማሳሰቢያ

በኮሎምቦስ ኦሃዮ ለምትገኙ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን በሙሉ። በቅድሚያ የአክብሮት ሰላምታችን እናቀርባለን። በከተማችን ኮሎምቦስ ኦሃዮ የሚገኙ ጥቂት የወያኔ አባላትና በጥቅም የታወሩ፣ለሆዳቸው ያደሩ፣ ደጋፊዎቻቸው የካቲት አስራ አንድን (የካቲት 11) ማለትም በደደቢት ጫካ  የትጥቅ ትግል የጀመሩበት 35ኛ በዓላቸውን April 10/2010 ለማክበር ደፋ ቀና በማለት ላይ ይገኛሉ።

የካቲት 11 ቀን  ሃገራችን ኢትዮጵያ እንድትበጣጠስ መሰረት የጣሉበት፤

- የኢትዮጵያ ሕዝብ በዘር፣ በጎሣ፣ በክልልና በቋንቋ ለመለያየት ያሴሩበት፤
- የኢትዮጵያ ሉአላዊነትና አንድነት አደጋ ለመጣል የተሰባሰቡበት፤
- የኤርትራ ሕዝብ ከናት ሃገሩ ከኢትዮጵያ ለማስገንጠል ሁኔታዎች ያመቻቹበት፤
- የብዙ ንፁሃን ዜጎች ህይወት የቀጠፈና ደም ያቃባ፤ እስካሁን ድረስ እያወዛገበ ያለው ከጎንደርና ከወሎ ክ/ሀገር ለም የሆኑ ቦታዎች ከሕዝብ ፍልጎት ውጭ ለመንጠቅ እቅድ ያወጡበት፤ ከ80 ሚሊዮን በላይ ሕዝብ የሚገኝባት አገር ያለ ባሕር በር ያስቀረ ቀን በመሆኑ፡ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በሀዘን የሚያስባት ዕለት እንጅ ጮማ እየቆረጡ፡ ውስኪ እየተረጩ በጭፈራና በዳንኪራ የምናስባት ቀን ስላልሆነች ይህን ማሳሰቢያ እንድናወጣ ተገደናል።

እነዚህ እጃቸው በንጹሃን ደም የታጠቡ ጥቂት የወያኔ አባላት፡ ጉድና ጅራት ከበስተኋላ እንዲሉ፡ ወያኔ የፈጸመችው ግፍና በደል፣  ክህደትና፣ ሴራ፣ የድሮ የወያኔ አመራር አባላት ሳይቀሩ በግልጽ በመገናኛ ብዙሃን እየወጡ በማጋለጥና ከሕዝብ ጐራ እየተቀላቀሉ ባሉበት ሰዓት፣ ደርሶ የወያኔ ጋሻ ጃግሬ ለመሆን፡ ጫማ የሚልሱ ፍጡራን፡ በተመሩት የከተማ ቦታ፣ ለመደለያ በሰጧቸው የእርሻ መሬት ወይም ከቀረጥ ነፃ በሆነ መንገድ በሚያስገቧቸው፡ ትራክተሮች፡ ማረሻዎች ሆነ ሌላ ቁሳቁስ ሳይደለሉ ላንዴ ቆም ብለው ህሊናቸውን እንዲመረምሩና ከእውነተኛ ኢትዮጵያዊ ወገናቸው ጋር ግዜው ሳይመሽባቸው እንዲቀላቀሉ ወገናዊ ምክራችንን እንለግሳለን፡ ይህንን ቆራጥ እርምጃ ለመውሰደም ግዜው አሁን ነው እንላለን።

ከኔ በኋላ ሠርዶ አይብቀል እንዳለችው፡ እንስሳ ሆነው ዛሬ ይመቸኝ  እንጅ ስለነገ የነገው ሰው ይጨነቅበት በማለት፡ በዚች ጥቂቶች በሚደሰቱባት፡ ነገር ግን ብዙዎች በሀዘን የሚያስቧት እለት ለምትገኙ ሆድ አምላኮች" <u>እዝያም ሂደህ በላህ፣ እዚም መጥተህ በላህ፣ ሰው ታዘበህ እንጂ ሆድህን አልሞላህ"</u> በማለት በትዕዝብት ብቻ እንደማናያቹና የስም ዝርዝራችሁን በግልጽ በመገናኛ ብዙሃን በመጠቀም  የምናጋልጣችሁ መሆናችን በዚህ አጋጣሚ ልንገልጽላችሁ እንወዳለን።

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!! ሞትና ውድቀት ለወያኔና ደጋፊዎቻቸው።

በኰለምቦስ ኦሃዮ የምንገኝ አገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን። 4/5/2010